መፍረሻው ደረሰ የቆመው ጣዖት(ተስፋሁን ሞላ)



እራሱን ከፍ ከፍ፤
ከጥንት ጀምሮ የተከለከለን
ስርአቷ ተጣሰ የቤተ-ክርስቲያን
በሃያ አንደኛው በአለነበት ዘመን
እራሱን በሾመ በአባ ገ/መድህን።
    ምስሉን አቆመው በመድኃኔዓለም ቤት
    እሱን አስመስሎ ከግቢው ፊት ለፊት
    ሕዝቡም ተሳስቶ ሰገደ ለጣዖት
    ምህረትን ሳያገኝ የነፍሱን መድኃኒት
    ተመልሶ መጣ ተሸክሞ ኃጢአት።
እራሱን ከፍ ከፍ እንደ ዲያብሎስ
እኔ ነኝ ዳኛቸው የዓለም ንጉሥ
እጆቹን ዘርግቶ ብሎ ይናገራል ቆሞ እንደማይፈርስ።
    በምድር ወርቅ ቢለብስ በሰማይ ግን ትቢያ አመድን ይለብሳል
    ራሱን አጽዳቂ በጽድቅ ቀና መንገድ የሚሄድ ይመስል።
ብቻውን አይደለም አጃቢ ሞልቶታል
ከወንድም ከሴትም ተከታይ አፍርቷል
አብረው የሚጋዙ ሲሄድ ወደ ሲኦል
ቀኑ ትደርሳለች ዓመት ወራት ሳትል።
    ፈጣሪውን ንቆ፤
    ሳጥናኤልን መስሎ ቢያሳብጥ ልቡን
    መፍረስ መች ይቀራል ኢምንት መሆን
    ጨለማ ይገባል አያይም ብርሃን።
ከዚህ በላይ ያለችው ጽሁፍ ምስሉን እንዳቆመው ከማለፉ በፊት የተጻፈች ናት።

የተኩላውን ንጉሥ የሳጥናኤልን ሎሌ
ልቡን አቀለጠው እንደ ጨው አሞሌ።
የሚኖር መስሎት የተኩላው አባ
በጌታ ማደሪያ ሲዘምት በዋልድባ
ትናት ወደቀ አሉ ጉድጓድ ውስጥ ሊገባ።
ይኖራል የተባለው ለአምስት መቶ ዓመት
መፍረሻው ደረሰ የቆመው ጣዖት
የኢትዮጵያ አምላክ አወረደ መቅሰፍት
ልጅና አባቱን ሲያስተኛ በአንድነት
አደግዳጊው ሁሉ አደረበት ፍርሃት።
መቼ ተፈጸመ የወረደው መቅሰፍት
ገና ይቀጥላል እያለ አንድ ሁለት
ቤቱን ሳያጸዳ ከንዱን አይመልሳት
የፈጠራት ጌታ የዓለም መድኃኒት።
በመስቀል ላይ ሆኖ በደሙ ያነጻት
ኢትዮጵያን አይደለም ከዓለም የመረጣት።
ከእንግዲህ አቁሙ መሄዱን በቡድን
ትናት ተሸኝቶአል  አባ ገ/መድህን
ከዚያ እኩይ ልጁ ጋር ከአጠፋት ሀገርን።
ሥጋን ስታድልቡ ነፍሳችሁን ጎዳችሁ
ከርሳችሁን ልትሞሉ ኃጢአትን ሰራችሁ
ስትበሉ ስትጠጡ ዘመናዊ ሁናችሁ
ሌላም ስትሰሩ የምትኖሩ መስሎአችሁ
የእግዜርን ማደሪያ ከሁለት ከፍላችሁ
አያችሁት ሲወርድ መቅሰፍት ከቤታችሁ።
ከእንግዲህ ይብቃችሁ የስካሁኑ ጥፋት
ዘመናዊ መሆን ቁሞ በእግዚአብሔር ቤት
አይታችኋልና ከላይ ሲወርድ መቅሰፍት።
ጳጳስ መነኩሴ ቄስና ዲያቆን
እንዲሁም መምህራን ወንጌል ሰባኪያን
በውሸት ስብከት ማደናገር ሕዝብን
ሁለትም አይደለች አንዲት ናት ቤተ ክርስቲያን።
ተሎ ንስሐ ግቡ ሌላ ሳትጨምሩ
እየበዛ እንዳሄድ አንካሳው እውሩ
የሰላሙ መንገድ ሳይዘጋ በሩ
እግዜር አንዴ ወርዶአል ሊያድር በመንበሩ።